## የግል መገልገያ እቃ

1) ማንኛውም መንገደኛ፡-

   ሀ. በዚህ መመሪያ አባሪ በተደረገው ሠንጠረዥ "ሐ" ላይ የግል መገልገያ ዕቃ ተብለው በአይነት፣በመጠንና በብዛት ተለይተው የተዘረዘሩትን ዕቃዎች ቀረጥና ታክስ ሳይከፍል ወደ አገር ውስጥ ማስገባት ይችላል፡፡

   ለ. በዚህ መመሪያ አባሪ በተደረገው ሠንጠረዥ "መ" ላይ ለንግድ የማይውሉ የግል መገልገያ ዕቃ ተብለው በአይነት፣በመጠንና በብዛት ተለይተው የተዘረዘሩትን ዕቃዎች ቀረጥና ታክስ ከፍሎ ወደ አገር ውስጥ ማስገባት ይችላል፡፡

   ሐ. በዚህ መመሪያ አባሪ በተደረገው ሠንጠረዥ "ሐ" ላይ ወጪ የግል መገልገያ ዕቃዎች ተብለው በአይነት፣ በመጠንና በብዛት ተለይተው የተዘረዘሩትን ዕቃዎች ወደ ውጭ አገር ይዞ መውጣት ይችላል፡፡

2) ተመላሽ ኢትዮጵያዊ ፣ በተለያዩ ሙያዎች ኢትዮጵያ ዉስጥ ለማገልገል በህጋዊ መንገድ ተቀጥሮ ወይም በሌላ ህጋዊ ስምምነት ኢትዮጵያ ዉስጥ ለማገልገል የሚመጣ ትዉልደ ኢትዮጵያዊ ወይም የዉጭ አገር ዜጋ፣ መንግስት በሚያደርገው ልዩ ጥሪ የሚመጣ ኢትዮጵያዊ ወይም ትውልደ ኢትዮጵያዊ ወይም የውጭ አገር ዜጋ፣ ማንኛውም ኢትዮጵያ ውስጥ ኢንቨስት ያደረገ ትውልደ ኢትዮጵያዊ ወይም የውጭ ባለሀብት እና አንድ ዓመት እና ከዚያ በላይ በግል ስራ፣ በቅጥር ወይም በትምህርት ውጭ አገር የቆየ ኢትዮጵያዊ፡-

   ሀ. በዚህ መመሪያ አባሪ በተደረገው ሠንጠረዥ "ሠ" ላይ የግል መገልገያ ዕቃ ተብለው በአይነት፣በመጠንና በብዛት ተለይተው የተዘረዘሩትን ዕቃዎች ቀረጥና ታክስ ሳይከፍል ወደ አገር ውስጥ ማስገባት ይችላል፡፡

ለ. በዚህ መመሪያ አባሪ በተደረገው ሠንጠረዥ "ረ" ላይ ለንግድ የማይውሉ የግል መገልገያ ዕቃ ተብለው በአይነት፣በመጠንና በብዛት ተለይተው የተዘረዘሩትን ዕቃዎች ቀረጥና ታክስ ከፍሎ ወደ አገር ውስጥ ማስገባት ይችላል፡፡

ስለማስረጃ አቀራረብ

1) ተመላሽ ኢትዮጵያዊ፡-

ሀ/ በውጭ አገር የቆየበትን ጊዜ እና ጠቅሎ ወደ ኢትዮጵያ መመለሱን የሚገልጽ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተረጋገጠ (Authenticated) የመሸኛ ደብዳቤ ከነበረበት አገር ካለው ወይም የነበረበትን ሀገር ጭምር ከሚያገለግለው የኢትዮጵያ ኤምባሲ ወይም ቆንስላ ወይም ሚሲዮን ማቅረብ አለበት፡፡

ለ/ የኢትዮጵያ ሚሲዮን ከሌለበት አገር የሚመጣ ከሆነ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የመኖሪያ ፈቃዱን እና የሥራ ውሉን ሳያሰርዝ የመጣ መሆኑን በማጣራት በፓስፖርቱ ላይ በተለጠፈው ስቲከር ላይ ተሰርዟል (void) የሚል ማህተም በማድረግ የሚሰጠውን የመሸኛ ደብዳቤ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

2) ከስደት ተመላሽ፡-

ሀ/ ከስደት ተመላሽ በስደት በቆየበት አገር ካለው ወይም በስደት የቆየበትን ሀገር ጭምር ከሚያገለግለው የኢትዮጵያ ኤምባሲ ወይም ቆንስላ ወይም

ሚሲዮን የተሰጠውን መሸኛ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል አረጋግጦ ማቅረብ አለበት።

ለ/ የኢትዮጵያ ኤምባሲ ወይም ቆንስላ ወይም ሚሲዮን ከሌለበት አገር የሚመጣ ከሆነ ከደህንነት፣ ኢሚግሬሽንና የስደተኞች ጉዳይ ባለስልጣን ከስደት ተመላሽ መሆኑን የሚያረጋግጥ ደብዳቤ ማቅረብ አለበት።

ሐ/ በስደተኛነት ቆይቶ በላኪው ሀገር እና በኢትዮጵያ መንግስት መካከል በሚደረግ ስምምነት መሠረት ወደ ኢትዮጵያ የሚመለስ ከስደት ተመላሽ ከደህንነት፣ ኢሚግሬሽንና የስደተኞች ጉዳይ ባለሥልጣን ከስደት ተመላሽ መሆኑን የሚያረጋግጥ ደብዳቤ ማቅረብ አለበት።

3) <u>ባለሀብት</u>

ማንኛውም ኢትዮጵያ ውስጥ ኢንቨስት ያደረገ ትውልደ ኢትዮጵያዊ ወይም የውጭ ባለሀብት፣ ባለሃብት ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ከሚመለከተው የኢንቨስትመንት ኮሚሽን/ቢሮ ማቅረብ አለበት።

4) <u>አግባብ ካለው የመንግስት መ/ቤት ወይም ተቋም ጋር በተደረገ ስምምነት መሰረት በኢትዮጵያ ለማገልገል የሚመጣ ባለሙያ፦</u>

አግባብ ካለው የመንግስት መ/ቤት ወይም ተቋም ጋር በተደረገ ስምምነት መሰረት በኢትዮጵያ ለማገልገል የሚመጣ የውጭ አገር ነዋሪ ኢትዮጵያዊ፣ ትውልደ ኢትዮጵያዊ እና የውጭ አገር ዜጋ ባለሙያ ስምምነቱን ባደረገው የመንግስት መ/ቤት ወይም ተቋም የበላይ ኃላፊ የተፈረመ ደብዳቤ ማቅረብ አለበት።

5) <u>መንግስት በሚያደርገው ልዩ ጥሪ የሚመጣ</u>

መንግስት በሚያደርገው ልዩ ጥሪ መሰረት በኢትዮጵያ ለማገልገል የሚመጣ የውጭ አገር ነዋሪ ኢትዮጵያዊ፣ ትውልደ ኢትዮጵያዊ እና የውጭ አገር ዜጋ ባለሙያ በጥሪው መሰረት ኢትዮጵያን ለማገልገል መምጣቱን የሚያስረዳ ከነበረበት አገር ካለው ወይም የነበረበትን ሀገር ጭምር ከሚያገለግለው

የኢትዮጵያ ኤምባሲ ወይም ቆንስላ ወይም ሚሲዮን የተሰጠ እና በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተረጋገጠ (Authenticated) ደብዳቤ ማቅረብ አለበት፡፡

6) <u>በግል ሥራ ፣ በቅጥር ወይም በትምህርት ቆይቶ የሚመጣ</u>

በግል ስራ፣ በቅጥር ወይም በትምህርት ውጭ ሀገር ቆይቶ የሚመለስ ኢትዮጵያዊ ከመጣበት አገር ካሰው ወይም የመጣበትን ሀገር ጭምር ከሚያገለግለው የኢትዮጵያ ኤምባሲ ወይም ቆንስላ ወይም ሚሲዮን የተሰጠ በዚሁ ሀገር ውስጥ በግል ሥራ፣ በቅጥር ወይም በትምህርት የቆየ መሆኑን የሚያስረዳ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተረጋገጠ ደብዳቤ ማቅረብ አለበት፡፡

**ገደብ**

1) በዚህ መመሪያ አባሪ በተደረገው ሠንጠረዥ "ሠ" እና "ረ" የተመለከተ ማንኛውም ባለመብት የሚያስገባውን ዕቃዎች በሙሉ በአንድ ሰነድ አጠቃሎ ወደ ኢትዮጵያ በገባ በስድስት ወር ጊዜ ዉስጥ ማስገባት አለበት፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተ ባለመብት የግል መገልገያ ዕቃዎቹን በአየር መንገድ እና በየብስ አንድ ጊዜ፣ ሆኖም ከሁለቱ የማስጫኛ ዘዴዎች በአንዱ ብቻ መጠቀም ከፈለገ በየብስ ወይም በአየር መንገድ ሁለት ጊዜ ብቻ ማስገባት አለበት፡፡ ሆኖም በዚህ መመሪያ በተፈቀደው መብት ተጠቃሚ ሊሆን የሚችለው ለአንድ ጊዜ ብቻ ነው፡፡